Amharic

# SUBURBAN MARYLAND WELCOME BACK CENTER

FOR FOREIGN-TRAINED HEALTH PROFESSIONALS

## በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ወደ ስራ ዓለም እንዲመለሱ ይረዳል

## ምን?

የዌልካም ባክ ሴንተር ሰብ አርባን ሜሪላንድ ልዩ የሆነ ማእከል ሲሆን በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኙ ስደተኞችን የሙያና የግል ሀብቶቻቸውን በመጠቀም የጤና ሙያተኞች እጥረትን ለማሙዋላት፣የጤና ግብረሀይሎችን ለማብዛት፣ በተገቢው ደረጃቸው ሲሰሩ ላልቻሉ የጤና ባለሙያተኞች ወደ ስራ ሲመለሱ ተገቢውን የገቢ እድል ለመፍጠር እና የጤና ን አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ማስፋፋት ይጥራል።

## መቼ?

በ 2006 እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር የላቲኖ ሄልዝ ኢኒሽቲቭ (ሞንትጎሜሪ ካውንቲ ዲፓርትመንት ኦፍ ሄልዝ ኤንድ ሂውማን ሰርቪስስ) የሜሪላንድ የጤና ባለሙያተኞች የብቃት ማረጋገጫ ሂደትን ለማገዝ በውጭ ሀገር የሰለጠኑ የጤና ባለሙያዎች የሚባለውን ፕሮግራም ጀመረ።በ 2010 እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር ይህ ፕሮግራም “ዌልካም ባክ ሴንተር ኦፍ ሰብ አርባን ሜሪላንድ” የተባለ ሲሆን ይሄም ካገሪቱ ካሉት የ “ዌልካም ባክ ኢኒሽቲቭ” መረብ መካከል አንዱ ነው።

## የት?

ማእከሉ በሜሪላንድ በተለይም በ ሞንትጎሜሪ፣ ፕሪንስ ጆርጅስእና ፌሬድሪክ ካውንቲስ ለሚኖሩ እና ከየትኛውም ሀገር የመጡ የጤና ባለሙያተኞች ግልጋሎት የሚሰጥ ማእከል ነው።

## ለምን?

የትምህርት እና ሌሎች መረጃዎቻቸው በሌላ ሃገር የተረጋገጠላቸዉ በጣም ብዙ የተማሩ እና ልምድ ያካበቱ በሜሪላንድ የሚኖሩ ስደተኞች ባሁኑ ሰአት መስጠት ከሚገባቸው የጤና ሙያዊ ግልጋሎት ተገልለዋል ወይም በተገቢው ድረጃ እያግለገሉ አይደለም። ማእከሉ ከተለያየ አገር የመጡ የጤና ባለሙያውች የጤና አገልግሎት በተገቢው ደረጃ ላላገኘው ህብረተሰብ የጤና አገልግሎት በመስጠት እና በታካሚዎች እና በጤና ማእከላት ጥሩ ግኑኝነት በመፍጠር በጤናውን መስክ ወደተሻለ የህክምና ውጤት ለማምራት ያስችላሉ ብሎ ያምነል።

## እንዴት?

ማእከሉ ግቦቹን ለማሳካት የሚያከናዉናቸዉ ድርጊቶች እንደሚከተሉት ናቸዉ፤

- ምክር እና ድጋፍ፣ እንዲሁም ግለዊ ጉዳዮችን መምራት
- ትምህርታዊ ስልጠና፣ እንግሊዘኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ የመግባቢያ ቋንቋ እና የቦርድ ፈተና ዝግጅት
- በተግባር ስራ አማካኝነት ስለ ዩኤስ የጤና አገልግሎት አሰራር ልምድ መስጠት፣ በሜሪላንድ ሆስፒታል እና በሌሎች ጤና ጣቢያዎች ልምድ እና ተሞክሮዎችን ማካፈል
- ከጤና ጋር ለተገናኙ የስራ መስኮች ቅድመ ቅጥር አገለግሎት፣ ለቀጣይ ስራ እና ለስራ ብቁነት ስልጠና መስጠት
- ባህልን ያገናዘበ ለውጥ አምጭ የአመራር ችሎታ ስልጠና መስጠት።

## እነማን?

የማእከሉ አጋሮች የሎካል እና የስቴት መንግስታት፣ የትምህርት ማእከሎች እና ስራ የጤና ባለሙያዎች ቀጣሪ ድርጅቶችን ነው። እንዴት መሳተፍ እንደምትችሉ ማወቅ ለምትፈልጉ በስልክ ቁጥር 240-777-3168 ደውሉ፤ ወይንም የሚከተለዉን ድህረ ገጽ ተመልከቱት፡ http://www.lhiinfo.org/en-programs-and-activities/Welcome-Back-Center.asp.

April 2010